# ፍቅር መር አገልግሎት



ትምህርት 9 ለ ነሐሴ 23፣ 2018


“በብዙ መከራና ከልብ
ጭንቀት በብዙም እንባ
ጽፌላችሁ ነበርና፤ ይህም
እናንተን አብዝቼ
የምወድበትን ፍቅር
እንድታውቁ እንጂ
እንዳሳዝናችሁ አይደለም።”
(2 ቆሮንቶስ 2:4)



የጳውሎስን ሁለተኛ የቆሮንቶስ መልዕክት በጥልቀት ስናጠና ሐዋርያው ለቤተክርስቲያን ደህንነት ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጥ እንመለከታለን።

ምንም እንኳን በዚህች ኃጥያት በሞላባት ዓለም ውስጥ በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ፈጽሞ ቀላል ባይሆንም በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ግን በግልጥ ክርስቲያን ነኝ ማለት በራስ ላይ እንደመፍረድ ይቆጠር ነበር።

ጳውሎስ እነዚህን ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች ለመጋፈጥ እንዲዘጋጁና እኔነት በሌለበት ፍቅር አንድ እንዲሆኑ ሲመክራቸው ነበር። እኛም በዘመናችን “ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ” እንዴት መሆን እንደምንችል ከዚህ ምክር እንማራለን (2ቆሮ 2:16)።





- በመከራ ውስጥ የእግዚአብሔር ማፅናናት
- ቅድስናና ንጹህ ልቦና በአገልግሎት ውስጥ
- በጥበብ መመላለስ
- ይቅርታና መመለስ
- የክርስቶስ መዓዛ

# በመከራ ውስጥ የእግዚአብሔር ማፅናናት

"እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።" (2 ቆሮንቶስ 1:4)

ሁለተኛው የቆሮንቶስ መልዕክት ጳውሎስ ስለ ማጽናናት በሰፊው የሚናገርበት መልዕክት ነው። ቤተክርስቲያን በከባድ ጊዜ ውስጥ እያለፈች ስለነበር የቀደመው የጳውሎስ ደብዳቤ ወደ ሃዘን ስሜት ውስጥ ከትቷቸው ነበር።

ነገር ግን ያ ሃዘን "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ" ስለነበረ ወደ ንስሐ የሚመራ ነበር (2ቆሮ 7:10)። ስለዚህም ጳውሎስ ይህ ሃዘን እንዳያሸንፋቸው ደግሞም እንዲፅናኑ ይፈልግ ነበር።



እርሱ እራሱ ሕይወቱ በአደጋ ውስጥ ያለፈባቸውና ተስፋ የቆረጠባቸው ጊዜያት ነበሩ (2ቆሮ 1:8-10)። እግዚአብሔር ግን በነዚያ ጊዜያት አፅናንቶት ስለነበር ያገኘውን መጽናናት ለቤተክርስቲያን ማስተላለፍ ፈልጎ ነበር (2ቆሮ 1:6)።

## የእግዚአብሔር ማፅናናት

- ከፍርሃት ነፃ ያወጣናል
- ከዚህ በፊት እኛን የረዳበት ጊዜያትን ያስታውሰናል
- መከራን እንድንቋቋም ይረዳናል
- ወደ መንፈሳዊ ብስለት ያመራል
- ለሌሎች እንድንማልድ ያበረታታናል
- በእግዚአብሔር እንደተጽናናን እርስ በርሳችን እንጽናናለን

# ቅድስናና ንጹህ ልቦና በአገልግሎት ውስጥ

"ትምክህታችን ይህ ነውና፤ በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በሥጋዊ ጥበብ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቅድስናና ቅንነት በዚህ ዓለም ይልቁንም በእናንተ ዘንድ እንደኖርን የሕሊናችን ምስክርነት ነው።" (2 ቆሮንቶስ 1:12)


አንዳንድ ሰዎች ጳውሎስን ደካማ ነው ቆራጥም አይደለም እያሉ ይንቁት ነበር (2ቆሮ 10:10)። በዚህ ምክንያትና ደግሞም ምክሩን ይቀበሉት ዘንድ ጳውሎስ ራሱን ከነዚህ ክሶች መከላከሉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶት ነበር።



እንደ አንድ ተራ ሰው ራሱን ከምንም አይቆጥርም ነበር (ኤፌ 3:8) ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ንጹህ ህሊና እንዳለው በድፍረት መናገር ችሏል (2ቆሮ 1:12)።



ባህሪው በቤተክርስቲያን ውስጥም ሆነ ውጪ ቅዱስ መሆኑና ልቦናውም ንጹህ እንደሆነ እርሱና ጓደኞቹ በእርግጠኝነት ይመሰክሩ ነበር።



ይህን ተከትሎ የጳውሎስ ጽሁፎች ከድብቅ ሴራ የጸዱ ነበሩ። ስለዚህም ጽሁፎቹን በቅድስናና በንጹህ ልቦና አውድ እንዲያነቡና እንዲቀበሉት ተስፋ አድርጎ ነበር። ጽሁፎቹ ለነርሱ ካለው ፍቅርና መልካም እንዲሆንላቸው ካለው ፍላጎት የመነጩ እንደሆኑ እንዲረዱለት ይፈልግ ነበር (2ቆሮ 1:13-14)።

# በጥበብ መመላለስ

“እኔ ግን ልራራላችሁ ስል እንደ ገና ወደ ቆሮንቶስ እንዳልመጣሁ በነፍሴ ላይ እግዚአብሔርን ምስክር እጠራለሁ።” (2 ቆሮንቶስ 1:23)



ጳውሎስ በመጀመሪያው መልዕክቱ ሊጓዝበት ያቀደውን መንገድ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ነግሯቸው ነበር (1ቆሮ 16:5-11):

ኤፌሶን → መቄዶንያ → ቆሮንቶስ → ይሁዳ

ከዚያም ቀጥሎ በላከው ደብዳቤ ሁለት ጊዜ እንደሚጎበኛቸው አስታውቋቸው ነበር (2ቆሮ 1:15-16) (ይህ ደብዳቤ አሁን ጠፍቷል 2ቆሮ 7:8) :

ኤፌሶን → ቆሮንቶስ → መቄዶንያ → ቆሮንቶስ → ይሁዳ

ቢሆንም ግን መንገዱን ቀይሮ የመጀመሪያውን ጉብኝት ሊያስቀር ወስኖ ነበር (2ቆሮ 1:23)። ይህን ማድረጉ አንዳንዶች ጳውሎስ ያልሰከነና ወላዋይ ነው ብለው እንዲተቹት መርቷቸው ነበር። ሀሳቡን የቀየረው ለምንድን ነው?





በቆሮንቶስ ከነበሩት ችግሮች አንፃር የጳውሎስ መገኘት በጣም አስፈላጊ ነበር። ነገር ግን ለቆሮንቶስ ሰዎች በነበረው ፍቅር ምክንያት በዚያ የሚነሳበትን ተቃውሞ ላለመጋፈጥ መወሰኑን ያሳየናል (2ቆሮ 2:1-4)።

# ይቅርታና መመለስ

"እናንተ ግን ይቅር የምትሉትን እኔ ደግሞ ይቅር እለዋለሁ፤ እኔም ይቅር ካልሁ፥ ይቅር ያልሁትን ስለ እናንተ በክርስቶስ ፊት ይቅር ብዬአለሁ"
(2 ቆሮንቶስ 2:10)

ጳውሎስ ወደ ጢሮዓዳ ሲጓዝ ቲቶ ደግሞ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። ጳውሎስ ከጢሮዓዳ ተነስቶ ወደ መቄዶንያ ሄደ። ነገር ግን በጢሮዓዳ ሳለ ቲቶ ስለ ቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ዜናን ሊነግረው ስላልተገናኘው እጅጉን ተጨንቆ ነበር (2ቆሮ 2:12-13)።





ትንሽ ቆይቶ ቲቶ ጳውሎስን ሊገናኘው ወደ መቄዶንያ መጣ። ቤተክርስቲያኑቱም የጳውሎስን ተግሳጽ በደስታ መቀበሏን ነበረው (2ቆሮ 7:5-9, 13-16)።



መፍትሄ ከሚፈልጉ ችግሮቻቸው አንዱ የቤተክርስቲያንን ደንብ በተመለከተ ነበር። ሐዋርያውን በመታዘዝ ደንብ ለጣሱት አካላት ተግሳጽ ደርሶ እነርሱም ተግሳፁን ተቀብለውት ነበር። አሁን ደግሞ ጳውሎስ ቀጣዩን እርምጃ እንዲወስዱ ይጠይቃቸው ጀመር፤ እርሱም ይቅርታና መመለስ ነው (2ቆሮ 2:5-11)።

# የክርስቶስ መዓዛ

"በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና፤"
(2 ቆሮንቶስ 2:15)



በጢሮዓዳ ወንጌልን በስኬታማ መልኩ ይሰበክ ዘንድ እግዚአብሔር "ስለከፈተለት በር" እየመሠከረ ጳውሎስ በውዳሴና በድል እንዲህ እያለ አመሠገነ: "ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን" (2ቆሮ 2:14)።

የክርስቶስ እውቀት ልክ መዓዛው እንደሚያውድ ሽታ ለሁሉም ነፍስ ይደርሳል። ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲሁም ለእኛ ይህ የዘላለም ሕይወት መዓዛ ነው። ነገር ግን ጥሪውን ላልተቀበሉት ደግሞ የሞት ሽታ ይሆንባቸዋል (2ቆሮ 2:15-16)።





ጳውሎስ ይህን ተከትሎ በሚመጣው ኃላፊነት ላይ በማተኮር መልዕክቱ ያልሰሙትን ለማዳን ሲባል የግል ጥቅምን ወደ ጎን በመተው በትህትና ሊሰበክ እንደሚገባ ያስረዳል (2ቆሮ 2:17)።

“ይህ ታማኝ መልዕክተኛ በቆሮንቶስ አማኞች መካከል አስገራሚ ለውጥ ስለመከሰቱ የምስራችን ይዞ መጥቶ ነበር። ጳውሎስ በመልዕክቱ የሰጠውን መመሪያ ብዙዎች ተቀብለው ከኃጢያታቸው ንስሃ ገብተው ነበር። ህይወታቸው ክርስትናን የሚያሰድብ መሆኑ ቀርቶ ተግባራዊ የሆነ ፈሪሃ እግዚአብሔርን በኃይል የሚያሳይ ምሳሌ ሆኖ ነበር።[…]

በመለኮት ጸጋ ተጽዕኖ ከልብ የሚመጣው ንስሃ ወደ ኑዛዜና ኃጥያትን ወደ መተው ያመራል። ሐዋርያው በቆሮንቶስ አማኞች ህይወት ውስጥ ታይቷል ብሎ ያወጀው ፍሬ እንዲህ አይነቱን ነበር።

EGW (The Acts of the Apostles, pp. 324)